በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ




# ከጁላይ 1-31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

# እንዲሁም

# ከኦገስት 1-31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና

# ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2026


አዲስ አበባ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፈዉ የጁላይ ወር በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 33.2፣ ሀዋሳ 35.6፣ 56.7፣ በሃር ዳር 52፣ 44.4፣ 61.5፣ ኮምቦልቻ 35.8፣30.4፣ ደበረ ማርቆስ 30፣ ቢሾፍቱ 33.1፣ 32፣ 35.1፣ ጎንደር 40.1፣ 34.4፣ ጎሬ 38.5፣ 31፣ ጅማ 96.3፣ 38.6፣ 37.6፣ ነቀምት 38፣ 61፣ 38.6፣ 50.7፣ ሮቤ 30.4፣ አዴት 36፣ አይራ 36፣ 47.4፣ አማን 51.9፣ 30.5፣ አምባ ማሪያም 50.2፣ 42.6፣ 38.6፣ አምደወርቅ 37.6፣ አንገር ጉትን 33.2፣ 40፣ አርጆ 32.8፣ አርሲ ሮቤ 40፣ አሶሳ 39.5፣ 62.3፣ አፅቢ 40.7፣ አይከል 32፣ 52.፣ በደሌ 52፣ ባቲ 65፣ ቦሬ36.6፣ 42፣ 36.8፣ ቡሂ 39.7፣ 34.2፣ ቡለን 61፣ 35.4፣ 40፣ 30፣ 70፣ ቡሬ 45፣ 58.8፣ 76.2፣ ቻግኒ 30፣ ጨፋ 60፣ ጭፍራ 61.2፣ ጭራ 70፣ 35፣ ዳሊፋጊ 38.2፣ደባርቅ 31፣ ደበረ ብርሃን32.7፣ ደበረ ታቦር 34.4 48.3፣ ደበረ ወርቅ 44.1፣ 52.8፣ ደምቢ ዶሎ 30.5፣ 31.5፣ 36.3፣ 35.2፣ ፊቼ 38.8፣ 31.6፣ 43.7፣ ፉኙዶ36.6፣ 48፣ ጋምቤላ 65.6፣ 80፣ ገለምሶ 34.5፣ ጊምቢ 43.1፣ 55.4፣ 50.4፣ ጉንዶ መስቀል 31.7፣ 35.6፣ 49.3፣ ካቺሴ 44.4፣ እምድብር 31.4፣ ላሊበላ 90፣ ሊሙገነት 44፣ 62.7፣ 33፣ ማጀቴ 38.4፣ ማንኩሽ 60.2፣ ማሻ 30.6፣ ማሃል ሜዳ 47.6. 30፣ መካነሰላም 35.2፣ መተማ 44.8፣ ንፉስ መዉጫ 48.7፣ አዳማ 30.9፣ ነጆ 39.7፣ ፓዌ 32.2፣ ሰኮሩ 32፣ ሰንቃጣ 30.5፣ ሲርንቃ 36.8፣ 30.5፣ ሽሬ 37.5፣ 39.9 ሻሁራ 33.8፣ ሻምበ 34.2፣ 40.8፣ ሾላገበያ 50.7፣ ተርጫ 48፣ ወገልጤና 40፣ ወረኢሉ 47፣ 36፣ 46፣ ይትኖራ 38.3፣ ባቱ 35.5፣ 67.5፣ አባጃራ 32.4፣ አባይ ሸለቆ 32.3፣ 37.1፣ አቦሞሪንጋ 36.3፣ 44.7፣ 36.9፣ አዳሚቱሉ 41.2፣ አዲስ ዘመን 38.6፣ 39.9፣ አጋሮ 32.2፣ አቃስታ 30.6፣ አንኮበር 35፣ አሺ 32.4፣ 32፣ አሸሬ 37.8፣ 31.1፣ አሶሳ 30.5፣ አታንጎ 46.2፣ 37.7፣ ባምቢስ 45.2፣ ቢላምቢሎ 32.8፣ 35.7፣ 38.5፣ ቡልቂ 36.6፣ 36.1፣ 47.4፣ 33.2፣ 45.2፣ ጨፌዶንሳ 31.2፣ 30.7፣ ደበረ ሲና 39.9፣ 80.2፣ 35.1፣ ዲጋን 39.8፣ 62.1፣ ደነባ 50.2፣ 30.3፣ ደንጎለታ 32.1፣ እርብቲ 47.9፣ እነዳባጉና 30.6፣ 38፣ ጋላይ 33.2፣ ጋሸና 60.7፣ ጊናገር 36.4፣ ጊሽራቤል 44፣ 45.2፣ ጎብየሬ 35.6፣ ጉበቲ 47.8፣ ጉጉፍቱ 38.2፣ 49.6፣ 30.2፣ 36.8፣ 39.6፣ 75.5፣ ጉንዶ በረት 46፣ 30፣ ሐገረ ሰላም 36፣ ሃይቅ 78.8፣ ሃሮ 30.2፣ 30.5፣ 30፣ 30.2፣ 30.4፣ 30.5፣ 40.6፣ ሆሮዶዮ 30፣ ከሚሴ 50.5፣ ቅዳሜ ገቤ39.9፣ 36.6፣ 56.4፣ ኮሶበር 30.5፣ 36.4፣ ኩልመስክ 37.7፣ 30.2፣ ማያንሳ 39.4፣ መካነእየሱስ 44.6፣ ማርዬ 51፣ 83.1፣ ሞላሊ 48.7፣ ኦሞናዳ 38.6፣ 31.2፣ 32.5፣ 30.5፣ ኦንጋ 33.4፣ 30፣ ሸንዲ 46.5፣ ስቆጣ 35.4፣ ሲቦ 34.2፣ 45.3፣ ተርኮዲ 38.2፣ ትንሹመጢ 37.2፣ ጽገሬዳ 31.3፣ መንደር13 34.2፣ 32.4፣ 30.4፣ 32.4፣ 32፣ 30.2፣ መንደር11 46.5፣ ወልዲያ 30፣ ዉቅሮ 63፣ ወርቃምባ 34.7፣ እንዲሁም ገምቢ 47.5፣ 46.9 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። ነበራቸዉ፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የጁላይ ወር በ127 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡

ባለፈዉ የጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታና ጎፋ፣ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ61-570 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በጁላይ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ምስራቅና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ከአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታና ጎፋ፣ አዲስ አበባ ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ የተቀራረበ እና በጥቂት የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ጁላይ 1 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ጁላይ 1 እስከ 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ጁላይ 1 እስከ 31/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁላይ ወር በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም የተገኘው ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻልም አልፎ ከጁላይ ወር ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ፤ ከኤፕሪል ወር ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና ከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር በጎ ጎን ነበረው (ካርታ 4)።


## 1.3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁላይ ወር በአብዛኛቹ የሃገራችን ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ እጅግ ከፍተኛ የሚደርስ የገፀ-ምድር የውኃ ፍሰት የነበራቸው ሲሆን፣ በተለይም በባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞ ጊቤና ተከዜ ተፋሰሶች የነበረው እጅግ ከፍተኛ የውሃ ፍሰት ከገጸ ምድር አልፎ የከርሰ ምድር የውኃ ሃብት ክምችትን በማሻሻል፣ እንዲሁም በላይኛውና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ እና በአፋር ደናክል ተፋሰሶች የነበረው ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገጸ ምድር የውኃ ሽፋን የተፋሰሱን የውኃ ይዘት በማጎልበት ወደ ተለያየ የሰው ሰራሽም ይሁን የተፈጥሮ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውኃ መጠን በመጨመር ረገድ አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደነበረው የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ። በአንፃሩ በኦጋዴን፣ በታችኛው አዋሽ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በመካከለኛውና የታችኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ደረቅ የአየር ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በኦገስት ወር ውስዋ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የኦገስት ወር ከተቀሩት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን አካቶ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ወር ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በምዕራብ አጋማሽ በአብዛኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ200-400 ሚ.ሜ እና በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከ400 ሚ.ሜ በላይ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ18-30 ለሚደርሱት ቀናት ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ከ6-20 ቀናት ያህል እስከ 300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል።


### 2.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

በመደበኛ ሁኔታ የኦገስት ወር ካለፉት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በመጠንም ሆነ በሥርጭት በከፍተኛ መጠን የሚያደርስበት ወር ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለተከታታይ ሰዓትና ቀናት የሚዘንብበትና በተጨማሪም በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የሚስተዋልበት ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለወንዞች ሙላትና ቅጽበታዊ ጎርፍ የሚከሰትበት ወር ነዉ፡፡


በመጪው የኦገስት ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተሻሻሉ ሊሄዱ እንደሚችሉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥለዉ ወር ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዌ፤ አሶሳ፤ ካማሺ ዞኖች እና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከጋምቤላ ክልል ንዌር፣ አኝዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ(ካርታ 15 )፡ ፡ በተጨማሪም ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ላይ በመነሳት፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፉን እና ኤረር ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ጋቢ፣ ማሂ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

Total Rainfall (mm) for 1-31, 2026 Aug 2026




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1 እስከ 31/2026
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 1 እስከ 31/2026
የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ

Ethiopian Meteorology I

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኦገስት ወር በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብና የመካከለኛዉ የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚኖረው እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የረዥም ጊዜ ሰብሎች እድገትና ፍሬ ለማፍራት፤ ዘግይተዉ ለሚዘሩ የአጭር ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች የዉሃ ፍላጎትን ለማሟላት እና ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላም በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ የእርጥበት መብዛት ጋር ተያይዞ በረባዳማ አካባቢዎች ውሃ በሰብል ላይ መተኛት፣ የመሬት አቀማመጡ ከፍታ ባላቸውና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ የመሬት መንሸራተትና በጎርፍ የመጠቃት እንዲሁም እርጥበት በሚበዛባቸው አካባቢዎች የሰብል በሽታ እና የአረም መስፋፋት ሊከሰት ይችላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች እና ከፊል አርሶ አደሮች እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት ሰብሎች በጎርፍ እንዳይጠቁ እና በማሳ ላይ ውሃ እንዳይተኛ የጎርፍ መቀልበሻዎችንና ከማሳ ውስጥ ውሃን ማንጣፈፊያ ቦዮችን ማዘጋጀት እንዲሁም የፀረ-አረም እና የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱና የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል። በሌላ በኩል በመደበኛ ባህሪያቸዉ የእርጥበት እጥረት በሚያጋጥማቸዉ አካባቢዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን እንዳይከሰት የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋልና የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጭው የኦገስት ወር በአብዛኛው መረብጋሽ፣ ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው እና መካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና በጥቂት የላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የሃገራችን ተፋሰሶች በዚህ ወር ከፍተኛ የሆነ የገጸ-ምድር የውኃ ሃብት ግብዓትና ፍሰት የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከሚኖረው ተደጋጋሚ ዝናብና እርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአፈር ውስጥ ውሃ ሰርጎ

መግባትን በማሳደግ የከርሰ ምድር የውሃ ሃብት ግብዓት እንዲኖር አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከሚኖር ከባድ እና ተደጋጋሚ የዝናብ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች እና ለጎርፍ መፈጠር አመቺ በሆኑ በከተማም ሆነ በተጋላጭ  አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ፣ የወንዞች ሙላትና ከገደብ በላይ መፍሰስ የማስከተል አቅም ሊኖረው ይችላል። በተጨማሪም በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ በመካከለኛውና ታችኛው አዋሽ እንዲሁም የታችኛው ስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መካከለኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡

ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et